# የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን

# የምግብ ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 360/2013

ሰኔ 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ ገፅ

መግቢያ ........ 3

ክፍል አንድ ........ 4

ጠቅላላ ........ 4

1. አጭር ርዕስ ........ 4

2. ትርጓሜ ........ 4

3. የተፈፃሚነት ወሰን ........ 6

ክፍል ሁለት ........ 7

ምግብ ስለ መመዝገብ ........ 7

4. አጠቃላይ ........ **Error! Bookmark not defined.**

5. የአመዘጋገብ ሂደት ........ 9

6. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ በከፍተኛ ደረጃ ለብልሽት ተጋላጭ የሆነ የምግብ ምርቶች ስለመመዝገብ ........ 9

1) በከፍተኛ ደረጃ ለብልሽት ተጋላጭ የሆነ የምግብ ምርቶች ስለመመዝገብ ........ 9

2) ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ በዝቅተኛ ደረጃ ለብልሽት ተጋላጭ የሆኑ የምግብ ምርቶች ስለመመዝገብ ........ 13

7. በሀገር ውስጥ የሚመት ምግብ ምዝገባ ........ 13

8. ስለ ቅድመ-ማሳወቅ ........ 14

9. የምዝገባ ለውጥ፣ ዳግም ምዝገባና እድሳት ........ 15

10. ምግብ ስለ ማስተዋወቅ ........ 16

11. ስለ አገልግሎት ክፍያ ........ 16

12. ስለ አስተዳዳራዊ እርምጃ አወሳሰድ ........ 16

13. ስለ ቅሬታ አቀራረብና ምላሽ ........ 16

14. ተፈጻሚት የማይኖራቸው ህጐች ........ 16

15. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ........ 17

## መግቢያ

ለህብረተሰቡ የሚቀርብ ምግብ ደህንነት ለማረጋገጥ በምግብ ምዝገባና ፈቃድ ላይ ያተኮረ ጠንካራ እና ውጤታማ የምግብ ደህንነት ቁጥጥር ስርአት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በሀገራችን ተመርተውም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምግቦች ለህብረተሰቡ ምግብነት አገልግሎት ከመዋላቸው በፊት ምንጫቸው አውቆ፤ ጥራታቸውንና ደህንነታቸውን በማረጋገጥ የገበያ ፈቃድ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ህብረተሰቡ ለገበያ የሚቀርቡ ምግቦች ምንጫቸውን በማወቅ ህጋዊ የሆኑ ምግቦችን ህጋዊ ካልሆኑ ምግቦች የሚለይበት በቂ መረጃ እንዲያገኝ እና ህገ-ወጥ የምግብ ንግድ ዝውውር ለመቆጣጠር የሚደረገውን እንቅስቃሴ በመረጃ የተደገፈ እንዲሆን ለማድረግ፤

በሕገ-ወጥ ምግብ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን የጤና ችግር ከወዲሁ ለመከላከል እና የምግብ ደህንነት ችግር ከማጋጠሙና በህብረተሰቡ ላይ የከፋ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠትና አሰቀድሞ ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በምግብና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 71(2) መሰረት ይህ መመርያ ወጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የምግብ ምዝገባ መመሪያ ቁጥር360/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በአዋጁ ቁጥር 1112/2011 ላይ የተቀመጡት ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡-

1) "ምግብ" ማለት በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ ተዘጋጅቶ ለሰው ምግብነት የሚውል ነገር ሲሆን ገበያ ላይ የዋለ ወይም ለህብረተሰብ አገልግሎት የቀረበ እጽዋት፣ የዕጽዋት ውጤት እና የዕንስሳ ውጤት፣ የምግብ ጨው፣ ውኃ፣ አልኮል ወይም ሌላ መጠጥ እና ምግብ ለማምረት ወይም ለማከም የሚውል ማንኛውም ንጥረ-ነገር የሚያካትት ሆኖ መድኃኒት፣ የውበት መጠበቂያ እና ትምባሆን አያካትትም፤
2) "ምዝገባ" ማለት በዚህ መመርያ ላይ ዝርዝራቸው በዕዝል 3 (1 እና 2) አባሪ በተደረገው መሰረት ምዝገባ ለሚካሄድበት ምግብ ለህብረተሰብ ሽያጭ ከመቅረቡ በፊት እንደ ምግቡ አይነትና ባህሪ የተቀመጡ መስፈርቶች መ□ላታቸውን በማረጋገጥ የሚሰጥ የቅድመ ገበያ ፈቃድ ነው፤
3) "ቅድመ-ማሳወቅ" ማለት ዝርዝራቸው በዚህ መመሪያ ዕዝል 3 (3) የተጠቀሱትን ከውጪ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ወይም በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የምግብ ዓይነቶች ለህብረተሰቡ ሽያጭ አገልግሎት ከመቅረባቸው ወይም ወደ ሀገር ከመግባታቸው አስቀድሞ በባለሰልጣኑ እንዲያውቅ የማድረግ ሂደት ነው፤
4) "ምግብ አምራች" ማለት ምግብ በፋብሪካ ደረጃ በማምረት ለገበያ ሽያጭ የሚቀርብ ተቋም ሆኖ ባህላዊ ምግቦችን (ሽሮ፣ በርበሬ እና መሰል ምርቶች) የሚያዘጋጁ አነስተኛ ተቋማትን አይጨምርም፤
5) "በቅድሚያ የታሸገ ምግብ" ማለት ለሽያጭ ከመቅረቡ በፊት በምግብ አምራች የታሸገ ምርት ነው፤

6) “የምግብ ጭማሪ” ማለት አግባብ ባለው የደህንነት መስፈርት መሠረት ምግብን ለማጣፈጥ፣ ለማቅለም፣ ሳይበላሽ ለማቆየት፣ ለማሳመር ወይም ለተመሳሳይ ሌላ ዓላማ በምግብ ላይ የሚጨመር ንጥረ-ነገር ነው፤

7) “የሕጻናት ምግብ” ማለት አግባብ ባለው ደረጃ መሠረት ከእንስሳት ወይም እጽዋት ተዋጽኦ በፋብሪካ ደረጃ የሚመረት ምግብ ሆኖ እድሚያቸው ከ6 ወር እስከ 3 ዓመት ለሆኑ ሕጻናት ምግብነት በፋብሪካ ደረጃ የሚዘጋጅ ምግብ ነው፤

8) “ማሚያ ምግብ” ማለት ማንኛውም የመደበኛ አመጋገብ የንጥረ-ምግብ ፍላጎት ለሟሟላት ሲባል የሚዘጋጅ የንጥረ-ምግብ ወይም በሰውነት ተፈጥሯዊ አሰራር ላይ ውጤት ያላቸው የቫይታሚን፣ ማዕድን ወይም ሌሎች ንጥረ-ነገሮች በነጠላ ወይም በጣምራ የሚገኙበትና በተወሰነ መጠን እንዲወሰድ ታስቦ በካፕሱል፣ በእንክብል፣ በዱቄት፣ በፈሳሽ፣ በጠብታ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ የሚዘጋጅ ምግብ ነው፤

9) “የምግብ ጥራትና ደህንነት ማረጋገጫ ስርዓት” ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት ምዝገባ የሚካሄድበት ምግብ አምራች ድርጅት ምግቡን ጥራትና ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ለማምረት እንዲችል ተግባራዊ የሚያደርገው በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ እውቅና የተሰጠው የአሰራር ሥርዓት ነው፤

10) “የሶስተኛ ወገን የምርት ብቃት ማረጋገጫ” ማለት የምግቡ አምራች ድርጅት የሚያመርተው ምርት የሀገሪቷን ደረጃ ስለማሟላቱ እውቅና ባለው አካል የሚሰጥ የምርት ደህንነት ማረጋገጫ ሰነድ ነው፤

11) “የሶስተኛ ወገን የላብራቶሪ ምርመራ ውጤት” ማለት ለምዝገባ የሚቀርበው ምግብ የተቀመጠውን የጥራትና ደህንነት መስፈርት የሚያ□ላ ስለመሆኑ እውቅና በተሰጣቸው ላቦራቶሪዎች ተመርምሮ ሲረጋገጥ የሚሰጥ የምግብ ላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ውጤት ነው፤

12) “በልዩ ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውል የምግብ አይነት” ማለት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በተለያዩ የስራ ዘርፍ ተሰማርተው ለሚገኙ የውጪ ዜጎች በተወሰነ መጠንና ጊዜ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውሉ የምግብ አይነቶች ናቸው፤

13) “በ24 ሠዓት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል የምግብ አይነት” ማለት በ24 ሰዓት ውስጥ ለምግብነት ካልዋለ ለብልሽት ተጋላጭ የሚሆን የምግብ አይነት ነው፤

14) “በከፍተኛ ደራጃ ለብልሽት ተጋላጭ የሆኑ ምግቦች” ማለት ከምግቦቹ ተፈጥሯዊ ይዘትና ባህሪ አንጻር በቀላሉ ለበሽታ አምጪ ተህዋሲያን ዕድገት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ እና አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል የሚጠቀምባቸው የምግብ አይነቶች ሆነው በዚህ መመሪያ ዝርዝራቸው በዕዝል 3 (1) አባሪ የተደረጉ የምግብ አይነቶችን ያጠቃልላሉ፤

15) “በዝቅተኛ ደረጃ ለብልሽት ተጋላጭ የሆኑ ምግቦች” ማለት ከምግቦቹ ተፈጥሯዊ ይዘለትና ባህሪ አንጻር ለበሽታ አንጪ ተህዋሲያበን እድገት ምቹ ሁኔታን የማይፈጥሩ የምግብ አይነቶች ሆነው ዝርዝራቸው 3 (2) አባሪ የተደረጉ የምግብ አይነቶችን ያጠቃልላሉ፤

16) “ከፍተኛ ለውጥ (major variation)” ማለት በምርቱ ጥራትና ደህንነት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ሊያሳድር የሚችል እንደ ማምረቻ ቦታ፣ ግብዓትና የምግብ ጭማሪ ፣ የምርት ማሸጊያ አይነት ፣ የምርት ቅንብር፣ የአመራረት ሂደት፣ የምርት የመጠቀሚያ ጊዜ፣ የምርት መስፈርት (product specification) እና ሌላ ተመሳሳይ ለውጥ ነው፤

17) “አነስተኛ ለውጥ (minor variation)” ማለት በምርቱ ጥራትና ደህንነት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ የማያሳድር የምርት ተወካይ፣ የምርት አርማ ፣ የምርት የንግድ ስም ፣ የምርት የተጣራ ክብደት እና ሌላ ተመሳሳይ ለውጥ ነው፤

18) “የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት በምግብ ንግድ ሥራ ላይ ለመሰማራት ለሚፈልግ ድርጅት አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የሥራ ፈቃድ ነዉ፤

19) “ባለስልጣን” ማለት የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፤

20) “አዋጅ” ማለት የምግብ እና የመድኃኒት አሰተደደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 ነው፤

21) “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

22) በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸ አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በፋብሪካ ደረጃ ተቀነባብረው ወይም ተመርተው ለሀገር ውስጥ ገበያ በሚቀርቡ የምግብ ምርቶች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ሆኖ በህጻናት እና ማሟያ ምግቦች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

## ክፍል ሁለት

## ምግብ ስለ መመዝገብ

4. **ጠቅላላ**

1) ለህብረተሰቡ የሚቀርብ እና ዝርዝሩ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ የተደረገ ማንኛውም ምግብ በባለሥልጣኑ ሳይመዘገብ እና የገበያ ፈቃድ ሳያገኝ ለሽያጭ ማቅረብ፣ ማስተዋወቅ ወይም የምርት ይዘት፣ አይነትና ሂደት ለውጥ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

2) ማንኛውም ለምዝገባ የሚቀርብ ምግብ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የደህንነት መስፈርቶችን ማሟለት አለበት፡፡ ይህ ከሌለ በአለም አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ ደህንነት መስፈርቶችን ማሟለት ይኖርበታል፡፡

3) ለምዝገባ የሚቀርቡ ሰነዶች በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ መቅረብ አለባቸው፡፡ ሰነዶቹ ከእንግሊዘኛ ወይም አማርኛ ቋንቋ ውጪ በሌሎች ቋንቋዎች የተዘጋጁ ከሆኑ የሰነዶቹ ህጋዊ ትርጉም ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

4) ለምዝገባ የቀረቡት ምርቶች የምግብ ጭማሪ (Food additives) ጥቅም ላይ የሚያውሉ ከሆኑ የምግብ ጭማሪው ለተባለው አገልግሎት መዋል ስለመቻሉ ባለሰልጣኑ ሀገራዊ ወይም አለም አቀፍ ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ ያረጋግጣል፡፡

5) ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶች የተሟሉ መሆናቸውን ሰነድ በመገምገም፣ የምርቱ ናሙና በላቦራቶሪ ፍተሻ በማድረግና እንዳስፈላጊነቱ አምራች ድርጅቱ የመስክ ምልከታ በማካሄድ የምግቡን ደህንነት ሲያረጋግጥ ምግቡን በመመዝገብ የገበያ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

6) ማንኛውም ሰዉ ምግብን ለማስመዝገብ አመልክቶ ከባለስልጣኑ እስከ 3 (ሶስት) ጊዜ ማብራሪያ ተጠይቆ ተገቢውን ምላሽ የማይሰጥ ከሆነ በድጋሚ እንደ አዲስ ማመልከት አለበት፡፡

7) ማንኛውም ሰዉ ምግብን ለማስመዝገብ አመልክቶ ከባለስልጣኑ ተጨማሪ ማብራሪያ ከተፃፈበት ቀን ጀምሮ እስከ 6 (ስድስት) ወር ድረስ ምላሽ ካልሰጠ ከዚህ ቀደም

ያስገባው መረጃ እንደተሰረዘ ተቆጥሮ ምዝገባዉን እንደ አዲስ መጀመር ይኖርበታል፡፡

8) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በምዝገባ ወይም በማሳወቅ ሂደት ውስጥ ሳያልፉ ለህብረተሰቡ ሽያጭ ሊቀርቡ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ ምግቦች፡፡

ሀ) ለግለሰብ ጥቅም የሚውሉ፤

ለ) ለሳይንሳዊ ምርምሮችና ለናሙናነት የሚውሉ፤

ሐ) በ24 ሠዓት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ፤ እና

መ) በልዩ ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውሉ ምግቦች

## ክፍል ሦስት

## በውጭ ሀገር ተመርተው ወደ ሀገር የሚገቡ የምግብ ምርቶች ስለ መመዝገብ

5. **የአመዘጋገብ ሂደት**

1) ማንኛውም ሰው ዝርዝራቸው ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ የተደረጉ ምግቦችን ለማስመዝገብ የተቀመጠውን ቅፅ (እዝል 1) በመሙላት ለገቢ ምግቦች በአንቀፅ 6 ላይ የተዘረዘሩ መረጃዎችን በማያያዝ ማቅረብ አለበት፡፡

2) በአንድ አምራች ድርጅት የተመረተ ተመሳሳይ ይዘት፣ መጠንና ማሸጊያ ያለው የምግብ ምርት በተለያዩ አመልካቾችና አስመጪዎች ለምዝገባ ሲቀርብ በባለስልጣኑ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

3) በውጭ ሀገር ተመርተው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምግቦች አንዴ በባለስልጣኑ ከተመዘገቡ ወይም ከታወቁ፤ ከአምራች ድርጅቱ ጋር ህጋዊ ስምምነት የተደረገበት ዉል (Agency Agrement) በማቅረብ እና የቀረበው ውል አሳማኝ መሆኑ ሲረጋገጥ ምርቱን ወደ ሀገር ማስገባት ይቻላል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 የተገለጸው ይህ መመሪያ ከወጣበት ከ6 ወር በኋላ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

6. **ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ በከፍተኛ ደረጃ ለብልሽት ተጋላጭ የሆነ የምግብ ምርቶች ስለመመዝገብ**

1) **በከፍተኛ ደረጃ ለብልሽት ተጋላጭ የሆነ የምግብ ምርቶች ስለመመዝገብ**

ሀ) ማንኛዉም ሰዉ በውጭ ሀገር ተመርተው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምግቦችን ለማስመዝገብ ከአምራች ድርጅቱ ጋር ህጋዊ የስምምነት ውል ያደረገበትን ሰነድ (Agency Agrement) ማቅረብ አለበት፡፡

ለ) የዚህ አንቀጽ ንኡስ-አንቀጽ 1 (ሀ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረበው ህጋዊ የስምምነት ውል (Agency Agrement) ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መስፈርቶች መያዝ ይኖርበታል፡፡

I. ምርቱ ከሶስተኛ ወገን አምራች ጋር በሚደረግ ውል መሰረት የተመረተ ከሆነ በውል ሰጪና ተቀባይ መካከል ያሉ ሀላፊነቶች መጠቀስ አለባቸው፤ በተጨማሪም በውል ሰጪና ሀገር ውስጥ ያለ አስመጪ ወይም ተወካይ መካከል የተደረገ ህጋዊ ስምምነት መኖር አለበት፡፡

II. የተደረገው ህጋው ስምምነት በሁለቱም ድርጅቶች የተፈረመ እና ማህተም ያረፈበት መሆን አለበት፡፡

III. በስምምነት ውሉ ላይ ማናቸውም በምግቡ ምክንያት የሚመጡ የጤና እክሎች ሲኖሩና ምርቱ ላይ ጥራትና ደህንነት በሚጓደልበት ጊዜ ሀላፊነት የሚወስድ አካል እንዲሁም የምርቱ ደህንነት ሲጓደል ከገበያ መሰብሰብ እንዳለባቸው በግልፅ መጠቀስ ይኖርበታል፡፡

IV. በሁለቱም የተደረገው የስምምነት ውል ሲፈርስ አስመጪው ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

ሐ) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1፣ ሀ) እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰዉ ዝርዝራቸው ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ የተደረጉ እና በውጭ ሀገር ተመርተው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምግቦችን ለመጀመሪያ ጊዜ ለማስመዝገብ ፡-

I. በዚህ መመሪያ ላይ በቅፅ (እዝል 1) የተያያዘውን ቅፅ መሙላት፤

II. በምርት ስሪት ሀገር ተቆጣጣሪ ተቋም ምርቱን ለማምረት የተሰጠ እውቅና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ወይም የገበያ ፈቃድ / free Sale certificate/፤

III. የምግቡ አምራች ድርጅት ተግባራዊ ያደረገው እውቅና ባለው ተቋም የተሰጠ የምግብ ደህንነት ማረጋገጫ ስርዓት ሰርተፊኬት፤

IV. በሃገር ዉስጥ እዉቅና ካላቸዉ ላቦራቶሪዎች የተሰራ የላቦራቶሪ ዉጤት ወይም የሶስተኛ ወገን ላቦራቶሪ ወይም እነዚህን ማቅረብ ካልተቻለ የእዉቅና ሰርተፍኬት ካለዉ ከራሱ ከአምራቹ ላብራቶሪ ለምዝገባ የቀረበው ናሙና ምርመራ ውጤት፤

V. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ለ፣IV) ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የምርት ላቦራቶሪ ውጤቱ የምርቱ ናሙና በምዝገባ ወቅት ማምጣት የማይችል ከሆነ ምርቱ መግቢያና መውጫ ኬላ ላይ በሚደርስበት ወቅት ናሙና ተወስዶ የተመረመረው ውጤት ማቅረብ ይችላል፤

VI. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ለ፣V) ላይ የተጠቀሰውን አማራጭ የሚወስድ ከሆነ ምርቱ መግቢያና መውጫ ኬላ ላይ በሚደርስበት ወቅት ናሙና ተወስዶ የተመረመረው ውጤት ብቻ ተቀባይት ይኖረዋል፤

VII. ምርቱን ለማምረት እንደ ግብዓት የሚውሉ ጥሬ እቃዎች ደህንነት፣ ዝርዝር እና ምንጭ የሚገልጹ ሰነዶች፤

VIII. የምግብ ምርቶች የመጠቀሚያ ጊዜን ለመወሰን በ Zone 4a (Real time stability study 30±2 $^{0}$C 65±5 RH እና Accelerated time stability study 40±2 $^{0}$C 75±5 RH) የተሰሩ ጥናቶች መረጃ፤

IX. ለምዝገባ የቀረበው ምርት የእንስሳት ምርቶችና ተዋፆኦ ከእንስሳ ወደ ሰው ከሚተላለፉ በሽታዎች ነፃ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ሰርተፊኬት አግባብነት ካለው ተቋም ወይም ከአምራች ድርጅቱ፤

X. ባለስለጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለምዝገባ የቀረበው ምርት ናሙና ሀገራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ደረጃ ሚሟላቱ የላቦራቶሪ ምርመራ ሊያርግበት ይችላል፤

XI. ለእነዚህ ምርቶች የመስክ ግምገማ ሊካሄድ ይችላል፤

XII. የምርቱን ማሸግያ ደህንነት የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ አለበት፡፡

መ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ለ፣VIII) የተጠቀሰውን ማሟላት ያልቻለ ተቋም ግዴታዎችን በጽሁፍ በመግባት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ማሟላት አለበት፡፡

ሠ) ማንኛውም ለምዝገባ የሚቀርብ የምርት ናሙና ገላጭ ፅሁፍ በጉልህ የተፃፈና የሚነበብ፣ የማይለቅ እና በአማርኛ ወይም በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተፃፈ ሆኖ፡-

I. የምግቡን የንግድ ስም፤
II. የምግቡ የወል ስም፤
III. በምግቡ ውስጥ ያለው የምግብ ንጥረ-ነገር ዝርዝርና መጠን በሰንጠረዥ፤
IV. በምርት ወቅት ጥቅም ላይ የዋሉ የምግብ ግብዓት ስም ዝርዝር፤
V. ምርቱ የተመረተበት ሀገርና የአምራች ወይም የአስመጪ ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ፤
VI. የተመረተበት እና መጠቀሚያ ጊዜው የሚያበቃበት ቀን ፤
VII. የምርቱ መለያ ቁጥር ፤
VIII. የምርቱ የተጣራ መጠን /ክብደት/፤
IX. ምርቱ የበለፀገ ምግብ ከሆነ የበለጸገበትን ንጥረ ነገር የሚያሳይ ግልፅ ፅሁፍ፤
X. የተጨረረ ምግብ ከሆነ መጨረሩን የሚያሳይ ግልፅ ፅሁፍ፤
XI. ምግቡ ልውጠ ህያው የሆኑ ግብዓቶችን በምርት ወቅት ከተጠቀመ ልውጠ ህያው መሆኑን የሚገልፅ መረጃ፣
XII. ለአለርጂክ የሚያጋልጡ ግብዓቶችን በምርት ወቅት ከተጠቀመ ይህንኑ የሚገልፅ መረጃ፤
XIII. እንደ ምግቡ ባህሪ የአጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ የሚገልፅ መረጃ መያዝ አለበት፡፡

ረ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (መ፣ (VI)) ስር የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

I. ለትኩስ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች፤
II. የአልኮል መጠናቸው ከ10 በመቶ በላይ የሆኑ መጠጦች፤
III. የተለያዩ ኮሚጣጤዎች፤
IV. ስኳር፤
V. የስኳር መጠናቸው ከ35 በመቶ በላይ የሆኑ ከረሜላዎች፣ ማስቲካዎች እና ሌሎች ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው የምግብ አይነቶች ምርቶቹ ከታሸጉበት ወይም ከተመረቱበት ቀን ውጪ የመጠቀሚያ ጊዜ የማይጠየቅባቸው የምግብ አይነቶች ይሆናሉ፡፡

2) ***ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ በዝቅተኛ ደረጃ ለብልሽት ተጋላጭ የሆኑ የምግብ ምርቶች ስለመመዝገብ***

*ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ በዝቅተኛ ደረጃ ለብልሽት ተጋላጭ የሆኑ የምግብ ምርቶች በተመለከተ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ* 1 (*ሐ፣* (VIII)) *የተጠቀሰውን ሳይጨምር በዚህ አንቀጽ ላይ የተጠቀሱ መስፈርቶች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡*

## ክፍል አራት

## በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምግቦች ስለመመዝገብ

7. ***በሀገር ውስጥ የሚመት ምግብ ምዝገባ***

1) *ማንኛውም ዝርዝሩ በዚህ መመሪያ ላይ አባሪ የተደረገ እና በሀገር ውስጥ የሚመረትና ለህብረተሰቡ የሚቀርብ ምግብ ለሽያጭ ከመቅረቡ በፊት በባለስልጣኑ ለማስመዝገብ ፡-*

*ሀ*) *በዚህ መመሪያ ላይ በቅፅ* (*እዝል* 1) *የተያያዘውን ቅፅ መሙላት፤*

*ለ*) *በባለስልጣኑ ተቆጣጣሪዎች ምርቱን ለማምረት የተሰጠ የእውቅና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት፤*

*ሐ*) *የምግቡ አምራች ድርጅት የውስጥ ደህንነት ማረጋገጫ ስርዓት ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን የሚያሳይ የኦዲቲንግ ኢንስፔክሽን ሪፖርት፤*

*መ*) *አስገዳጅ ደረጃ ለወጣላቸው ምርቶች የአስገዳጅ ደረጃ ምልክት ለመጠቀም ከሶስተኛ ወገን የተሰጠው ሰርተፊኬት፤*

*ሠ*) *በባለስልጣኑ ባለሞያዎች ወይም በሶስተኛ ወገን የምርቱን ናሙና በመውሰድ በሃገር ዉስጥ እዉቅና ካላቸዉ ላቦራቶሪዎች የተሰራ የላቦራቶሪ ዉጤት ወይም የሶስተኛ ወገን ላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት፤*

*ረ*) *ምርቱን ለማምረት እንደ ግብዓት የሚውሉ ጥሬ እቃዎች ዝርዝር እና ምንጭ የሚገልጹ ሰነዶች፤ እንዲሁም በራሱ ግብዓቶችን ከውጭ ሀገር የሚያስገባ ከሆነ የቅድመ የማሳወቅ ሂደትን ማለፍ ይኖርበታል፤*

*ሰ*) *ለምዝገባ የቀረበው ምርት ናሙና፤ እና*

ሽ) የምግብ ምርቶች የመጠቀሚያ ጊዜን ለመወሰን በ Zone 4a (Real time stability study 30±2 $^{0}$C 65±5 RH and Accelerated time stability study 40±2 $^{0}$C 75±5 RH) የተሰሩ ጥናቶች መረጃ መቅረብ አለበት፤

ቀ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (ሽ) የተጠቀሰውን ማሟላት ያልቻለ ተቋም ግዴታዎችን በጽሁፍ በመግባት በ1 (አንድ) ዓመት ጊዜ ውስጥ ማሟላት አለበት።

2) በሀገር ውስጥ የሚመረቱ በዝቅተኛ ደረጃ ለብልሽት ተጋላጭ የሆኑ የምግብ ምርቶች በተመለከተ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሽ) የተጠቀሰውን ሳይጨምር በዚህ አንቀጽ ላይ የተጠቀሱ መስፈርቶች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

3) የምግብ ምርት ገላጭ ፅሁፍን በተመለከተ በአንቀፅ 6 ንዑስ በአንቀፅ 1 (ሠ) ላይ ከተካተቱት መስፈርቶች በተጨማሪ ምርቱ አስገዳጅ ደረጃ የወጣለት ከሆነ የብሄራዊ አስገዳጅ ደረጃ ምልክት መለጠፍ ይኖርበታል፡፡

8. **ስለ ቅድመ-ማሳወቅ**

1) ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ ምረት ለሚያስመጣ ተቋም

ሀ) መግብያና መውጫ ኬላ ከመድረሱ ከ48 ሰአት በፊት በአዝል 2 (ቅጽ 1) የተጠቀሱ መረጃዎችን በመሙላት ማሳወቅ ያልበት ሆኖ ምርቱ ላይ መሰረታዊ ለውጥ ካላደረገ በስተቀር በየአመቱ የቅድመ ማሳውቅ ሰርተፊኬት ማሳድስ አለበት፤

ለ) በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ምርቱን ለማስመጣት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት፤

ሐ) የምግብ ምርት ገላጭ ፅሁፍን በተመለከተ በአንቀፅ 6 ንዑስ በአንቀፅ 1 (ሠ) ላይ የተጠቀሱ መስፈርቶችን ማሟላት ይኖርበታል፡፡

2) ለሀገር ውስጥ አምራች፡-

ሀ) በአዝል 2 (ቅጽ 2) የተጠቀሱ መረጃዎችን በአግባቡ መሙላት ይኖርበታል፤

ለ) ምርቱን ወደ ገበያ ከማቅረቡ በፊት ምርቱ ላይ መሰረታዊ ለውጥ ካላደረገ በስተቀር በየአመቱ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፤

ሐ) በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ምርቱን ለማምረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት፣

መ) የምግብ ምርት ገላጭ ፅሁፍን በተመለከተ በአንቀፅ 6 ንዑስ በአንቀፅ 1 (ሠ) ላይ የተጠቀሱ መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል።

9. **የምዝገባ ለውጥ፣ ዳግም ምዝገባና እድሳት**

1) ማንኛውም የተመዘገበ ምግብ በምርቱ ይዘትና ማሸጊያ ላይ ከፍተኛ (major) ወይም አነስተኛ (minor) ለውጥ ካልተደረገበት በስተቀር በየአራት ዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

2) የምግብ ምዝገባ ሰርተፊኬት ሲበላሽ፣ ሲጠፋ ወይም በተለያየ ምክንያት ከአገልግሎት ውጪ ሲሆን ለባለስልጣኑ በማሳወቅ ሊቀየርለት ወይም ምትክ ሊሰጠው ይችላል፡፡

3) በምርቱ ደህንነት ላይ ተፅእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ እንደ የማምረቻ ቦታ ፣ የግብዓትና የምግብ ጭማሪ ፣ የምርት ማሸጊያ አይነት ፣ የምርት ፎርሙሌሽን፣ የአመራረት፣ የምርት የመጠቀሚያ ጊዜ፣ የምርት ስፔሲፊኬሽን እና የምርት ማሸጊያና ሌሎች ተመሳሳይ ከፍተኛ ለውጦች ሲኖሩ ምርቱን እንደገና ለማስመዝገብ የለውጡን ምክንያት፣ የውስጥ ጥራትና ደህንነት ማራጋገጫ ስርዓት ሰርተፊኬት፣ የሶስተኛ ወገን ብቃጥ ማረጋገጫ ስረተፊኬት፣ ለውጥ የተደረገበት ለምዝገባ የቀረበው ናሙና በማቅረብ ከተቀመጠው መስፈርት አንጻር በመገምገም የምዝገባ ለውጥ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

4) በምርቱ ደህንነት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ የማያሳድሩ የምርት ተወካይ ፣ የምርት የንግድ ስም ፣ የምርት የተጣራ ክብደት እና ሌሎች ተመሳሳይ ለውጦች ሲኖሩ አመልካቹ ለባለስልጣኑ በማሳወቅ ብቻ የምርቱን የምዝገባ ለውጥ ማድረግ ይቻላል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 10. ምግብ ስለ ማስተዋወቅ

ማንኛውም የተመዘገበ ምግብ ማስተዋወቅ የሚቻለው በምግብ ማስተዋወቅ ቁጥጥር መመሪያ መሰረት ነው፡፡

### 11. ስለ አገልግሎት ክፍያ

ምግብን በማስመዝገብ የገበያ ፈቃድ ለማግኘት የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ በሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 370/2008 በወጣው የአግልግሎት ክፍያ ተመን መሰረት ይሆናል፡፡

### 12. ስለ አስተዳዳራዊ እርምጃ አወሳሰድ

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም የምግብ አምራች ወይም አስመጪ በባለስልጣኑ አዋጅ ቁጥር 1112/2011 እና በአስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ የተዘረዘሩት አስተዳደራዊ እርምጃዎች ሊወሰድበት ይችላል፡፡

### 13. ስለ ቅሬታ አቀራረብና ምላሽ

1) በዚህ መመሪያ መሰረት እርምጃ ስለተወሰደበት ምርት ቅሬታ ያለው ሰው በባለስልጣኑ የአስተዳዳራዊ እርምጃ አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ መሰረት በ1 (አንድ) ወር ጊዜ ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ አለበት፡፡
2) ቅሬታ የቀረበለት ቅሬታ ሰሚ አካል ቅሬታውን አጣርቶ በ 30 ቀናት ውሰጥ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

### 14. ተፈጻሚት የማይኖራቸው ህጎች

1) በዚህ መመሪያ ላይ የተደነገጉ ጉዳዮችን በተመለከተ መመሪያ ቁጥር 34/2009 ተሽሯል፡፡

2) ከዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር የማይጣጣም ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተካተቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

15. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከሰኔ 10 /2011 ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ሄራን ገርባ**

**የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን**

**ዋና ዳይሬክተር**

## አዝል 1

## ቅፅ1፡ ለገቢ ምግብ የምዝገባ መጠየቂያ ቅጽ

| ተ.ቁ | ርእስ | በአመልካች የሚሞላ |
|---|---|---|
| 1. | **አመልካች** | |
| | 1.1. ሥም | |
| | 1.2. ሙሉ አድራሻ | ክልል ..........................፣ ዞን/ክ/ከተማ /.................. ወረዳ/ቀበሌ .................. የቤት ቁጥር ........................ ስልክ ቁጥር፣ ኢ-ሜይል ወዘተ. የአካባቢው ልዩ መጠሪያ ካለ ይገለጽ ........................................................................................ |
| 2. | **የማመልከቻው አይነት**<br>አዲስ ☐ ዳግም ☐ የምዝገባ ለውጥ ☐ | |
| 3. | **የምግቡ አስመጪ/ተወካይ (importer/agent)** | |
| | 3.1. የድርጅቱ ሥም | |
| | 3.2. ሙሉ አድራሻ | ክልል ..........................፣ ዞን/ክ/ከተማ /.................. ወረዳ/ቀበሌ .................. የቤት ቁጥር ........................ ስልክ ቁጥር፣ ኢ-ሜይል ወዘተ. የአካባቢው ልዩ መጠሪያ ካለ ይገለጽ ........................................................................................ |
| | 3.3. የድርጅቱ ተወካይ ሥም | |
| 4. | **የምግቡ አምራች** | |
| | 4.1. ሥም | |
| | 4.2. ሙሉ አድራሻ | ሀገር .............................. ከተማ .............................. የመንገድ ቁጥር .............................. ስልክ ቁጥር .............................. ፋክስ .............................. የፖ.ሳ.ቁ .......................................... ኢ-ሜይል .................................... ድህረ ገፅ፣....................................... |
| | 4.3. የምግብ አምራች ተወካይ ሥም | |
| 5. | **የምግቡ ዝርዝር መረጃ** | |
| | 5.1. የምግቡ ስም (የወል፣ የንግድ ስም) | |
| | 5.2. የምርቱ ፊዚካላዊ ይዘቶች (ጠጣር፣ ፈሳሽ፣ ቀለም ሌሎች በዐይን የሚታዩ መስፈርቶች ወዘተ) | |
| | 5.3. የምርቱ የተጣራ የክብደት መጠን | |
| | 5.4. የምርቱ ማሸጊያ አይነት | |
| | 5.5. የምርቱ ተጠቃሚዎች | |
| | 5.6. የምርቱ የመጠቀሚያ ጊዜና አከመቻቸት ሁኔታ | |

| ተ.ቁ | ርእስ | በአመልካች የሚሞላ |
|---|---|---|
| | 5.7. የምርት የምግብ ንጥረ ነገር ዝርዝርና መጠን | |
| | 5.8. ጥቅም ላይ የዋሉ የግብዓትና የምግብ ጭማሪ ይዘት ዝርዝር | |
| 6. | **የምርት ምዝገባና ፍቃድ ሁኔታ** | |
| | 6.1. ምርቱ የተመዘገበበትና ፍቃድ ያገኘባቸው ሀገራት | |
| | 6.2. ወደ ገበያ እንዳይቀርብ የታገደባቸውና በጥራትና ደህንነት ጉድለት ከገበያ እንዲሰበሰቡ የተደረገባቸው ሀገራት ስም ዝርዝር | |
| 7. | **የአመልካች ማረጋገጫ** | |
| | እኔ ከዚህ በታች በፊርማዬ እንዳረጋገጥኩት ሁሉም የቀረቡት መረጃዎችና ሰነዶች ትክክለኛና ተዓማኒ መሆናቸውን እያረጋገጥኩ፣ ስህተት ሆኖ ከተገኘ ሙሉ ሃላፊነቱን የምወስድ መሆኑን አሳወቃለሁ፡፡<br><br>የድርጅቱ ተወካይ/ ባለቤት<br><br>ሥም: ______________________________<br><br>ፊርማ፡ ______________________________<br><br>በድርጅቱ ያለው ሃለፊነት፡ ________________________<br><br>ቀን: ______________________________<br><br>*የደርጅቱ ሕጋዊ ማህተም* ____________________ | |
| 8. | **ለቢሮ አገልግሎት ብቻ**<br><br>**በባለሥልጣኑ ተወካይ የሚሞላ** | |
| | ማመልከቻው የገባበት ቀንና ሰዓት | | |
| | ማመልከቻውን የተቀበለው ባለሙያ ስምና ፊርማ | |

## ቅጽ 2: ለሀገር ውስጥ ምግብ ምዝገባ መጠየቅያ ቅጽ

| ተ.ቁ | ርእስ | በአመልካች የሚሞላ |
|---|---|---|
| 1. | **አመልካች** | |

| ተ.ቁ | ርእስ | በአመልካች የሚሞላ |
|---|---|---|
| | 1.3. ሥም | |
| | 1.4. ሙሉ አድራሻ | ክልል ............................፣ ዞን/ክ/ከተማ /.................. ወረዳ/ቀበሌ ................ የቤት ቁጥር ......................... ስልክ ቁጥር፣ ኢ-ሜይል ወዘተ. የአካባቢው ልዩ መጠሪያ ካለ ይገለጽ ........................................................................................................ |
| 2. | **የማሳወቂ ሁኔታ**<br>አዲስ ☐ ዳግም ☐ ለውጥ ☐ | |
| 3. | **የምግቡ አምራች** | |
| | 3.1 . ሥም፡ | |
| | 3.2. ሙሉ አድራሻ | ክልል ............................፣ ዞን/ክ/ከተማ /.................. ወረዳ/ቀበሌ ................ የቤት ቁጥር ......................... ስልክ ቁጥር፣ ኢ-ሜይል ወዘተ. የአካባቢው ልዩ መጠሪያ ካለ ይገለጽ ...................................................................... |
| | 3.3. የምግብ አምራች ተወካይ ሥም | |
| 4. | **የምግቡ ዝርዝር መረጃ** | |
| | 5.1. የምግቡ ስም (የወል፣ የንምርት ስም (brand name)) ) | |
| | 5.2. የምርቱ ፊዚካላዊ ይዘቶች (ጠጣር፣ ፈሳሽ፣ ቀለም በዓይን የሚታዩ መስፍረቶች ወዘተ) | |
| | 5.3. የምርቱ የተጣራ ክብደት | |
| | 5.4. የምርቱ ማሸጊያ ዓይነት | |
| | 5.5. የምርቱ ተጠቃሚዎች | |
| | 5.6. የምርቱ የመጠቀሚያ ጊዜና አከመቻቸት ሁኔታ | |
| | 5.7 የምርት የምግብ ንጥረ ነገር ዝርዝርና መጠን /በሰንጠረዥ የቀረበ /tabular form/ | |
| | 5.8 ጥቅም ላይ የዋሉ የግብዓትና የምግብ ጭማሪ ይዘት ዝርዝር | |
| 6 | **የአመልካች ማረጋገጫ** | |

| ተ.ቁ | ርእስ | በአመልካች የሚሞላ | |
|---|---|---|---|
| | እኔ ከዚህ በታች በፊርማዬ እንዳረጋገጥኩት ሁሉም የቀረቡት መረጃዎችና ሰነዶች ትክክለኛና ተዓማኒ መሆናቸውን እያረጋገጥኩ፣ ስህተት ሆኖ ከተገኘ ሙሉ ሃላፊነቱን የምወስድ መሆኑን አሳወቃለው፡፡<br><br>የድርጅቱ ተወካይ/ ባለቤት<br><br>*ሥም፡* ______________________________<br><br>*ፊርማ፡* ______________________________<br><br>በድርጅቱ ውስጥ ያሎት ሃለፊነት፡ ______________________________<br><br>ቀን: ______________________________<br><br>*የደርጅቱ ሕጋዊ ማህተም* ______________________________ | | |
| 7 | **ለቢሮ አገልግሎት ብቻ**<br><br>**በባለሥልጣኑ ተወካይ የሚሞላ** | | |
| | *ማምልከቻው የገባበት ቀንና ሰዓት* | | |
| | *ማመልከቸውን የተቀበለው ባለሙያ ስምና ፊርማ* | | |

## እዝል 2

## ቅጽ-1: ለሀገር ውስጥ ምግብ ቅድመ-ማሳወቅ ማመልከቻ ቅጽ

| ተ.ቁ | ርእስ | በአመልካች የሚሞላ |
|---|---|---|
| 5) | **አመልካች** | |
| | 2.1 ሥም | |
| | 2.2 ሙሉ አድራሻ | ክልል ..........................፣ ዞን/ክ/ከተማ /............... ወረዳ/ቀበሌ ............... የቤት ቁጥር ........................<br>ስልክ ቁጥር፣ ኢ-ሜይል ወዘተ. የአካባቢው ልዩ መጠሪያ ካለ ይገለጽ<br>............................................................................................. |
| 2. | **የቅድመ-ማሳወቅ ሁኔታ** | አዲስ ☐ ዳግም ☐ ለውጥ ☐ |
| 3. | **የምግቡ አምራች** | |
| | 3.1 . ሥም፡ | |
| | 3.2. ሙሉ አድራሻ | ክልል ..........................፣ ዞን/ክ/ከተማ /............... ወረዳ/ቀበሌ ............... የቤት ቁጥር ........................<br>ስልክ ቁጥር፣ ኢ-ሜይል ወዘተ. የአካባቢው ልዩ መጠሪያ ካለ ይገለጽ ............................................................ |
| | 3.3. የምግብ አምራች ተወካይ ሥም | |
| | 3.4. የማምረት አቅም | |
| | 3.5. ተደራሽነት | |
| 4. | **የምግቡ ዝርዝር መረጃ** | |
| | 5.1. የምግቡ ስም (የወል፣ የንምርት ስም (brand name)) ) | |
| | 5.2. የምርቱ ፊዚካላዊ ይዘቶች (ጠጣር፣ ፈሳሽ፣ ቀለም በዓይን የሚታዩ መስፍረቶች ወዘተ) | |
| | 5.3. የምርቱ የተጣራ ክብደት | |
| | 5.4. የምርቱ ማሸጊያ ዓይነት | |
| | 5.5. የምርቱ ተጠቃሚዎች | |
| | 5.6. የምርቱ የመጠቀሚያ ጊዜና አከመቻቸት ሁኔታ | |
| | 7.7 የምርት የምግብ ንጥረ ነገር ዝርዝርና መጠን /በሰንጠረዥ የቀረበ /tabular form/ | |
| | 7.8 ጥቅም ላይ የዋሉ የግብዓትና የምግብ ጭማሪ ይዘት ዝርዝር | |
| 8 | **የአመልካች ማረጋገጫ** | |

| ተ.ቁ | ርእስ | በአመልካች የሚሞላ | |
|---|---|---|---|
| | እኔ ከዚህ በታች በፊርማዬ እንዳረጋገጥኩት ሁሉም የቀረቡት መረጃዎችና ሰነዶች ትክክለኛና ተዓማኒ መሆናቸውን እያረጋገጥኩ፣ ስህተት ሆኖ ከተገኘ ሙሉ ሃላፊነቱን የምወስድ መሆኑን አሳወቃለው፡፡<br><br>የድርጅቱ ተወካይ/ ባለቤት<br><br>*ሥም*: ______________________________<br><br>*ፊርማ*: ______________________________<br><br>በድርጅቱ ውስጥ ያሎት ሃለፊነት፡ ________________________<br><br>ቀን: ______________________________<br><br>*የደርጅቱ ሕጋዊ ማህተም* ____________________ | | |
| 9 | **ለቢሮ አገልግሎት ብቻ**<br><br>**በባለሥልጣኑ ተወካይ የሚሞላ** | | |
| | *ማምልከቻው የገባበት ቀንና ሰዓት* | | |
| | *ማመልከቸውን የተቀበለው ባለሙያ ስምና ፊርማ* | | |

## ቅፅ 2፡ ለገቢ ምግብ የቅድመ-ማሳወቅያ ማመልከቻ ቅጽ

| ተ.ቁ | ርእስ | በአመልካች የሚሞላ |
|---|---|---|
| 7. | **አመልካች** | |
| | 1.5. ሥም | |
| | 1.6. ሙሉ አድራሻ | ክልል ..........................፣ ዞን/ክ/ከተማ /................. ወረዳ/ቀበሌ ................. የቤት ቁጥር ........................ ስልክ ቁጥር፣ ኢ-ሜይል ወዘተ. የአካባቢው ልዩ መጠሪያ ካለ ይገለጽ ........................................................................................ |
| 8. | **የማመልከቻው አይነት** | አዲስ ☐ ዳግም ☐ የምዝገባ ለውጥ ☐ |
| 9. | **የምግቡ አስመጪ/ተወካይ (importer/agent)** | |
| | 3.1. የድርጅቱ ሥም | |
| | 3.2. የምግብ ማከማቻ መጋዘን ሙሉ አድራሻ | ክልል ..........................፣ ዞን/ክ/ከተማ /................. ወረዳ/ቀበሌ ................. የቤት ቁጥር ........................ ስልክ ቁጥር፣ ኢ-ሜይል ወዘተ. የአካባቢው ልዩ መጠሪያ ካለ ይገለጽ ........................................................................................ |
| | 3.3. የድርጅቱ ተወካይ ሥም | |
| 10. | **የምግቡ አምራች** | |
| | 4.1. ሥም | |
| | 4.2. ሙሉ አድራሻ | ሀገር ............................ ከተማ ............................ የመንገድ ቁጥር ............................ ስልክ ቁጥር ............................ ፋክስ ............................ የፖ.ሳ.ቁ ........................................ ኢ-ሜይል .................................... ድህረ ገፅ፣...................................... |
| | 4.3. የምግብ አምራች ተወካይ ሥም | |
| 11. | **የምግቡ ዝርዝር መረጃ** | |
| | 5.1. የምግቡ ስም (የወል፣ የንግድ ስም) | |
| | 5.2. የምርቱ ፊዚካላዊ ይዘቶች (ጠጣር፣ ፈሳሽ፣ ቀለም ሌሎች በዐይን የሚታዩ መስፈርቶች ወዘተ) | |
| | 5.3. የምርቱ የተጣራ የክብደት መጠን | |
| | 5.4. የምርቱ ማሸጊያ አይነት | |
| | 5.5. የምርቱ ተጠቃሚዎች | |
| | 5.6. የምርቱ የመጠቀሚያ ጊዜና አከመቻቸት ሁኔታ | |
| | 11.7. የምርት የምግብ ንጥረ ነገር ዝርዝርና መጠን | |

| ተ.ቁ | ርእስ | በአመልካች የሚሞላ | |
|---|---|---|---|
| | 11.8. ጥቅም ላይ የዋሉ የግብዓትና የምግብ ጭማሪ ይዘት ዝርዝር | | |
| 12. | **የምርት ምዝገባና ፍቃድ ሁኔታ** | | |
| | 8.1. ምርቱ የተመዘገበበትና ፍቃድ ያገኘባቸው ሀገራት | | |
| | 8.2. ወደ ገበያ እንዳይቀርብ የታገደባቸውና በጥራትና ደህንነት ጉድልት ከገበያ እንዲሰበሰቡ የተደረገባቸው ሀገራት ስም ዝርዝር | | |
| 9. | **የአመልካች ማረጋገጫ** | | |
| | እኔ ከዚህ በታች በፊርማዬ እንዳረጋገጥኩት ሁሉም የቀረቡት መረጃዎችና ሰነዶች ትክክለኛና ተዓማኒ መሆናቸውን እያረጋገጥኩ፣ ስህትት ሆኖ ከተገኘ ሙሉ ሃላፊነቱን የምወስድ መሆኑን አሳወቃለሁ፡፡<br><br>የድርጅቱ ተወካይ/ ባለቤት<br><br>ሥም፡ ____________________<br><br>ፊርማ፡ ____________________<br><br>በድርጅቱ ያለው ሃለፊነት፡ ____________________<br><br>ቀን: ____________________<br><br>*የደርጅቱ ሕጋዊ ማህተም* ____________________ | | |
| 10. | **ለቢሮ አገልግሎት ብቻ**<br><br>**በባለሥልጣኑ ተወካይ የሚሞላ** | | |
| | ማመልከቻው የገባበት ቀንና ሰዓት | | |
| | ማመልከቸውን የተቀበለው ባለሙያ ስምና ፊርማ | | |

**እዝል 3: የምግብ ዓይነቶች ዝርዝር ከምርቱ ባህሪ አንጻር**

## 1) High risk food products

1. Processed animal product
2. Processed sea foods
3. Processed fruit and vegetable
4. Processed Nuts
5. Therapeutic foods
6. Complementary foods (for more than 3 yrs Young children's)
7. Fortified foods (iodized salt, edible oil, flour, etc…)

## 2) Low risk food products

1. Crackers, Snack food and Confectionery products
2. Edible oils and Fats
3. Packed water
4. Soft drinks
5. Beers
6. Extruded products and Noodles

## 3) Notified food products

1. Hot sauce
2. Legume products
3. Packed Rice products
4. Processed seed (Corn, wheat, sorghum, barley, oat, etc ) products
5. Packed sugar
6. Bakery raw materials
7. Processed coffee and tea
8. Processed Spices
9. Alcohol (more than 10%) and liquor products
10. Vinegars and
11. other related food products not mentioned in category 1 and 2
12. Imported aid food products donated by governmental or non-governmental organizations.
13. Raw materials used for food production